በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሐገረ ስብከት ጽ/ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahdo Church Diocese of Northern California, Nevada, and Arizona Main Office

Date 6/10/2026
ሰካኔአሀጽ 6/10
Ref 104

በሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ለሚገኙ የኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክ አድባራት እና ገዳማት በሙሉ

ጉዳዩ ፤ የጸሎት እና ድጋፍ ጥሪ በአርሲ ሀገረ ስብከት ቤተ ክርስቲያን ላይ ለደረሰው ጥቃት እና ለተሰዉ ኦርቶዶክሳውያን

በቅድሚያ የአክብሮት ሰላምታችን በያላችሁበት ይድረሳችሁ በማለት በምሥራቅ አርሲ ሀገረ ስብከት በአሰኮ፣በሽርካ፣ በሆንቆሎ፣ በዋቤ እና በሙኔሳ ወረዳዎች በቅርቡ በኦርቶዶክሳውያን ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን ግድያ እና የቤተ ክርስቲያን መቃጠል ጉዳይ ሀገረ ስብከታችን በጽኑዕ ያወገዘ መሆኑን እየገለጽን በሀገረ ስብከታችን ባሉ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት የምትገኙ ካህናት ፣ መዘምራን እና መላው ምእመናን ከሰኔ 7 ወይም June 14 ጀምሮ በየአጥቢያችሁ የጸሎተ ምሕላ እና ፍትሐት አገልግሎት እንዲሰጥ እናሳስባለን።

በመጨረሻም ወገኖቻቸውን በሞት ላጡ እና የተፈናቀሉ ወገኖችን ለመደገፍ እንዲሁም በእሳት የተቃጠለችውን ቤተ ክርስቲያን ለመደገፍ አቅም የፈቀደውን የገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ እንድትተባበሩ እየጠየቅን የሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት አስተዳደር አካላትም ድጋፉን ወጥ እና ማእከላዊ ለማድረግ ወደ ሀገረ ስብከታችን የምግባረ ሰናይ አካውንት በማስገባት የድርሻችሁን እንድትወጡ ጥሪያችንን እናቀርባለን። አምላካችን እግዚአብሔር ይህን የቤተ ክርስቲያን መከራ በምሕረቱ ያሳልፍልን፣ የሞቱትን ነፍሶቻቸውን በመንግሥቱ ይቀበልልን፣ የተጎዱትንም በቸርነቱ ያጽናናልን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር

06/10/26

Ethiopian Orthodox Tewahedo Church of Northern California, Nevada and Arizona Archdioceses Head Office

Melake Gibhat Abba Haileyesus Gesese
General Menger the Diocese of Northern California, Nevada and Arizona Administrator of Debre-Mihret St ,Michael EOTC in Lasvegas

ግልባጭ: ለ ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
ለ ሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
ለ ሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ወረዳ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት በያሉበት